# ተከራዮች አቤቱታቸውን የሚያቀርቡበት ሂደት

ስለ አገልግሎት ወይም ስለ ባለደረባ ተከራይ አሠራር አቤቱታ ካለዎት በቶሮንቶ የማሕበረሰብ መኖሪያ [ኮሚኒቲ ሃውሲንግ] የሚገኘውን የመፍትሄ ሃሳቦች አፈላላጊ ቡድንን ማነጋገር ይችላሉ፡፡ የመፍትሄ ሃሳቦችን አፈላላጊ ቡድን [ሶሉሽንስ ቲም] የተከራዮችን ቅሬታዎች በፍትሃዊነት፣ በብቃት፣ ግልጽነት ባለው መንገድና በፍጥነት ለመፍታት ወደ ቲ ሲ ኤች ሲ የሚቀርቡትን አቤቱታዎች ሂደት ይቆጣጠራል፡፡

---

## የተለመዱ የአቤቱታ ፈርጆች

### ጸረ-ማሕበራዊ ባሕርይ



### ማሞቂያ/ማቀዥቀዣ



### ሊፍተሮች



### የጥገና ሥራ



### የውኃ ቧንቧ ሥራ



---

## ሦስቱ አቤቱታዎችን የማቅረብ ሂደቶች

### 1. ሪፖርት

አቤቱታዎን ወይም ቅሬታዎችን ለማሳወቅ፣ መፍትሄ አፈላላጊ ቡድናችንን በ solutions@torontohousing.ca ያግኙ ወይም በቴሌ. **416-981-6000** ደውለው ያነጋገሩ፡፡



### 2. ምርመራ

በአንድ የሥራ ቀን ውስጥ መፍትሄ አፈላላጊ ቡድኑ አቤቱታዎ የደረሰው መሆኑን ያሳውቃል፤ እንዲሁም ለቅሬታዎ የተመደበውን የኢዚ-ትራክ ቁጥር ያረጋግጣል፡፡ ከዚያም መመርመር ይጀምራሉ፡፡



### 3. ውሳኔ




የመፍትሄ ሀሳቦች አፈላላጊ ቡድን የእርስዎን አቤቱታ ለመፍታት ምን እንደ ተደረገ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ማብራርያ ይሰጣል፡፡ አቤቱታዎን ለመፍታት ከሰባት ቀናት በላይ የሚፈጅ ከሆነም የመፍትሄ ሀሳቦች አፈላላጊ ቡድን ጉዳይዎ ምን ላይ እንደ ደረሰ መግለጫ ይሰጣል፡፡

የመፍትሄ ሀሳቦች ቡድን ከሰጠው ውሳኔ ጋር ካልተስማሙ ቶሮንቶ የሚገኘውን የሕዝብ አቤቱታ ሰሚ ተቋም በ ombudsman@toronto.ca ኢሜይል በማድረግ ወይም በቴሌፎን ቁጥር **416-392-7062** በመደወል ማነጋገር ይችላሉ፡፡

---

# የመፍትሄ ሀሳቦች አፈላላጊ ቡድን ከደንበኞች እንክብካቤ ማዕከል ወይም ከህንጻ ሠራተኞች እንዴት ይለያል?

የደንበኞች እንክብካቤ ማዕከል ከክልል ቢሮዎችና ከአጥቢያ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ጋር አስተዳደርን እና የጥገና ሥራ ጥበቃን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ እርስዎን ለመርዳት እዚያ የሚገኙ ናቸው፡፡

የመፍትሄ ሀሳቦች አፈላላጊ ቡድን ደግሞ ቀደም ሲል በተከራዮች ሪፖርት የተደረጉና መፍትሄ ያላገኙ አቤቱታ ጉዳዮችን የመከታተል ኃላፊነት ያለው ነው፡፡

ይሁን እንጂ ተከራዮች ከሠራተኞች ጋር በሚኖራቸው መደበኛ ግኑኝነት ጉዳዮቻቸውና ፍላጎቶቻቸው በአግባብ እንዳልተያዙ ከተሰማቸው ቅሬታቸውን የሚያቀርቡበት የአቤቱታ ሂደትና አሠራር አለ፡፡

---

# አዎንታዊ ግብረ መልስን ስለ ማስገባት

ከ ቲ.ሲ. ኤች. ሲ ሠራተኞች በነበረዎት ግኑኘት ደስተኛ ከሆኑ እና ስለ አገልግሎቱ ምሥጋና ለማቅረብ ከፈለጉ ይህንንም ወደ መፍትሄ ሀሳቦች አፈላላጊ ቡድን መላክ ይችላሉ፡፡

---

# የመገናኛ መረጃ

የመፍትሄ ሀሳቦች አፈላላጊ ቡድን [ሶሉሽንስ ቲም]
**416-981-6000** ወይም **solutions@torontohousing.ca**

የድረገጽ እና የመስመር ቅጽ፡-
**torontohousing.ca/complaints**

ይህንን መግለጫ ጽሑፍ በተደራሽነት ይዘት ወይም በተተረጎመ መልኩ ለማግኘት ከፈለጉ፣ በቴሌ. ቁጥር **416-981-5500** ደውለው ያነጋግሩን ወይም በኢሜይል **help@torontohousing.ca** ያግኙን፡፡